# ቢዘገይም እውነታን መቀበል ከጥንካሬ ይቆጠራል

ዋሲሁን ከበደ 1/6/14

ሁሉን የማጥላላትና የማንቋሸሽ መጥፎ ፖለቲካዊ አካሄድ አገራችን ለጀመረችው የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታም ሆነ የፀረ-ድህነት ትግል የሚበጅ ባለመሆኑ አንዳንድ የአገራችን ተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች ከዚህ ጭፍን የጥላቻ አካሄድ ሊወጡ የሚገባ ይመስለኛል። አንዳንዴ ሳስበው የአገራችን ተቃዋሚ ሃይሎች መንግስት በምተሃት ከሰማይ ዳቦ ማዝነብ ቢችል እንኳን መልካም ነገር ነው ብለው መቀበል ይቸገራሉ። ለዚህ ማሳያ ይሆናሉ ያልኳቸውን አንዳንድ ነገሮችን እንደሚከተለው ለማንሳት እሞክራለሁ።

መንግስት አገራችን ከድህነትና ኋላ ቀርነት ተላቃ ህዝቦች መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ እንድትሰለፍ ለማድረግ ጠንክሮ በመስራቱ አገራችን የሚሌኒየሙን የልማት ግቦች ያሳካሉ ከተባሉት ጥቂት ከሰሃራ በታች ካሉ አገራት መካከል ግንባር ቀደም እንደሆነች የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የ2013 ዓመታዊ ሪፖርትን ማየቱ ተገቢ ይመስለኛል።

የመንግስታቱ ሪፖርት ላይ እንደተመለከተው እጅግ በርካታ የአለማችን አገራት ይህን የልማት ግብ ማሳካት ተስኖቸው ባሉበት ሲዳክሩ አንዳንዶች ደግሞ ባሉበት ደረጃ እንኳን መሰንበት አቅቷቸው የኋሊት እየተንሸራተቱ ያሉበትን ሁኔታም ገልጿል። ይሁንና አገራችን በተከተለችው የጠራ ፖሊሲና ስትራቴጂ አለም በኢኮኖሚ ቀውስ በምትዳክርበት ወቅት አገራችን በለሁለት አሃዝ እድገት በማስመዝገብ የሚሌኒየሙን የልማት ግብ ከሚያሳኩ አገራት መካከል በግንባር ቀደምትነት የምትጠቀስ ሆናለች።

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሚሌኒየም የልማት ግቡቦች ለማሳካት ከተቀመጡት ስምንት ነጥቦችን በማስላት ኢትዮጵያ 5.5 የሆነ ከፍተኛ ውጤት በማስመዝገብ ከሌሎች የልማት ግቡን ያሳካሉ ከተባሉ የአፍሪካ አገራት ማለትም ሩዋንዳ፣ ማላዊ፣ ጋናና ኡጋንዳ ጋር ስትነፃፀር ቀዳሚ እንደሆነችም ሪፖርቱ በይፋ አመላክቷል።

እንግዲህ ይህን ሪፖርት የአገሬ ተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች እንዴት ትመለከቱት ይሆን? ልብ በሉ ይህን ሪፖርት ያጠናቀረው የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮችና የፖለቲካ ሊቆቻቸው በመረጃ ምንጭነት ሲያቀለጳጵሱት የሚውሉት የአለም ባንክ ነው። የአለም ባንክ ተሳስቷል ትሉ

ይሆን? ወይስ ኢህአዴግ ጠንክሮ መስራት በመቻሉ አገሪቱ በእድገት ጎዳና መጓዟን አምናችሁ ትቀበሉ ይሆን? ወይስ ኢህአዴግ የተባበሩት መንግስታትን የሚያህል አለም አቀፍ ድርጅት እጅ በመጠምዘዝ ይህን ሪፖርት እንዲያዘጋጅ አስገድዶት ይሆናል ትሉ ይሆን? በእርግጠኝነት ሶስቱንም አማራጮች ለእናንተ መልካም በለመሆናቸው ልትቀበሏቸው አትችሉም። ምክንያቱም የቀረቡት ሁሉም አማራጮች የእናንተን ደካማነት የሚያጎሉ እንዲሁም በመረጃ ምንጭነት ስትጠቀሙበት የኖራችሁበትን ተቋም የሚያስተች በመሆኑ ይህን ሪፖርት አይታችሁ እንዳላያችሁ፣ ሰምታችሁ እንዳልሰማችሁ በመሆን ፈረንጆች By pass የሚሏትን አካሄድ የምትመርጡ ይመስለኛል።

ሶስቱም አማራጮች ለእናንተ መልካም አይሆኑም ያለኩበት ምክንያቶች ሳብራራቸው፤ የመጀመሪያው አማራጫችሁ ማለትም አለም ባንክ የተሳሳተ መረጃ አወጣ እንዳትሉ ይህን ተቋም ነጋ ጠባ በምንጭነት ስታጣቅሱት የምትውሉት እናንተ ነበራችሁ፤ ሁለተኛውን አማራጭ እንዳትሉ ኢህአዴግ ጠንክሮ ሰርቷል ማለት ደግሞ ሌላው የባሰ መጥፎ አማራጭ ይሆንባችኋል፤ ምክንያቱም ለኢህአዴግ የልማት ስራዎች እውቅና መስጠት ስለሚሆን። ሶስተተኛው አማራጭም ለእናንተ መልካም አይሆንም፤ ምክንያቱም ኢህአዴግ የአለም ባንክን እጅ ጠመዘዘ ማለት by default የኢህአዴግን ጥንካሬ መስካሪ ስለሚሆን ይህንንም አትፈልጉትም። ለዚህ ነው ከላይ እንዳነሳሁት ፈረንጆች By pass የሚሏትን አካሄድ የምትመርጡ ያልኩት።

ሌላው ተቃዋሚዎችና አጋሮቻቸው የሆኑት ሂዩማን ራይትስ ዎችና አምንስቲ ኢንተርናሽናልን የመሳሰሉት ድርጅቶች እየተረባረቡበት ያሉት ነገር መንግስት በአገራችን በግብርና ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ የሚያደርገውን ጥረት ነው። መንግስት የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት በአገራችን እንዲስፋፋና ለዜጎች የስራ እድል እንዲፈጠር በማድረጉ ከእነዚህ ድርጅቶች ተከታታይ የሆነ የሃሰት ውንጀላዎች እየተሰነዘሩበት ይገኛል።

በኢትዮጵያ ለእርሻ መዋል ከሚችለው መሬት ውስጥ እጅግ አነስተኛው አገልግሎት ላይ በዋለበትና ከ15 ሚሊዮን ሄክታር በላይ ያልታረሰ የእርሻ መሬት ባለበት ሁኔታ፣ መንግስት መሬትን ለውጭ ባለሃብቶች ለመስጠት ሲል ዜጎችን በሃይል ከይዞታቸው የሚያፈናቅልበት ምንያት ከቶ ሊኖር አይችልም። አገራችን ወደ እድገት ጎዳና ልትጓዝ የምትችለው ያለንን ውስን የተፈጥሮ ሃብት በአግባቡ መጠቀም ስንችል መሆኑንም ታሳቢ ማድረግ ተገቢ ነው።

በግብርና ላይ የሚካሄድ የውጭ ኢንቨስትመንት ለዜጎች የስራ እድል ከመፍጠሩም ባሻገር ለግብርና ስራችን መሻሻል ትምህርት የምንቀስምበት ዘርፍ በመሆኑ መበረታታት ሲገባው በሃሰት ውንጀላ

መጠመድ ተገቢ አካሄድ አይመስለኝም። በተጨማሪም የውጭ ቀጥታ አቨስትመንት መስፋፋት የአገራችንን የውጪ ምንዛሪ ክምችት በማሳደግ ጠንካራና ተፎካካሪ ኤኮኖሚን መገንባት የሚያስችል ዘርፍ ነው።

መንግስት የመሰረተ ልማትን በመላ አገሪቱ ፍተሃዊ በሆነ መልኩ ለማዳረስ ሲል ከፍተኛ ርብርብ እያደረገ እንደሆነ ይታወቃል። በአርብቶ አደሩ አካባቢም መንግስት ከፍተኛ የሆነ የመንገድ፣ ንፁህ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት፣ የትምህርትና የጤና ተቋማት ግንባታ፣ የሃይልና የቴሌኮሙዩኒኬሽን ዝርጋታ ወዘተ በትናንሽ የገጠር ቀበሌዎች ሳይቀር በማስፋፋት ላይ ይገኛል። አርብቶ አደሮች የእነዚህ መሰረተ ልማቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑና ዘመናዊ የአኗኗር ዘዴወችን እንዲላመዱ ለማድረግ መንግስት በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የሰፈራ የማሰባሰብ ስራም እያከናወነ እንደሆነ ይታወቃል።

እውነታው ይህ ሆኖ ሳለ የአገራችን ተቃዋሚዎችና አጋር የሆኗቸው እንደ ሂዩማን ራይትስ ዎችና አምንስቲ ኢንተርናሽናል ያሉ ድርጅቶች የሌለ የፈጠራ ወሬዎችን በመንዛት መንግስትን በመወንጀል ተግባር ተጠምደዋል።

ሌላው የአገራችን ተቃዋሚ ፓርቲዎች ነጠላ ዜማ የፖለቲካ ምህዳሩ ጠቧል፣ አሳታፊ አይደለም ወዘተ የምትለዋ ናት። አገራችን የመድበለ ፓርቲ ስርዓትን እውን ካደረገች ሁለት አስርት አመታት አስቆጥራለች። በህገ መንግስታችን በግልፅ እንደተደነገገው የስልጣን ብቸኛ ምንጭ ከምርጫ ኮሮጆ የሚገኝ የህዝብ ድምፅ መሆኑ እየታወቀ ይህ መንገድ አልሳካ ያላቸው አንዳንድ የአገራችን ተቃዋሚ ፓርቲዎች ሁለተኛ አማራጭ ብለው የሚያስቧትን አቋራጭ መንገድ ማለትም የቀለም አቢዮትን ሲማትሩ ማየት ከምርጫ 97 ወዲህ የተለመደ ክስተት ሆኗል።

የአገራችን ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች የህዝብን ቀልብ ሊገዛ የሚችል አማራጭ ፖሊሲና ስትራቴጂ ሊያቀርቡ ባለመቻላቸው በምርጫ አሸንፈው መውጣት አልቻሉም። የሚያስገርመው አንዳንዶቹ ፓርቲዎች የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ እንኳን በወጉ ስለሌላቸው አመራሮቻቸው እርስ በርስ በየመድረኩ ሲነታረኩ፣ ሲተማሙ፤ ደግሞም ግንባር ፈጠርን ብለው አንዴ ሲሰባሰቡ በብረሃን ፍጥነት ደግሞ ሲበታተኑ መመልከት የየእለት ክስተት ሆኗል።

እነዚህ ፓርቲዎች ችግራቸውን በመወያየት ከመፍታት ይልቅ ሁሌም ለችግራቸው ምንጭ ውጫዊ ሁኔታዎች ብቻ እንደሆኑ በማስመሰል “የፖለቲካ ምህዳሩ ጠቧል” የምትል ዘውትር የማትሰለቻቸው ዜማ ማቀንቀንን ይወዳሉ። ህገ መንግስቱ በጎናጸፋቸው ዴሞክራሲያዊ መብቶች ተጠቅመው

መደራጃታቸውን ዘንግተውት ይኸንኑ ነጻነትን የቸረ ስርዓትን  በየአደባባዩ መዝለፍና ማጣጣል የህግ ተጠያቂነትን ብቻ ሳይሆን የሚያስከትለው የሞራል ውድቀት መኖሩን ጭምር የሚያሳይ ነው።

በህዝብ  የሁንታ የተመሰረተ መንግስትን በነውጥና አመፅ መቀየር አለብን ብለው የሃይል እንቅስቃሴ ለማድረግ ጫካ የገቡ  ሃይሎችን በገንዘብም ሆነ በሃሳብ መደገፍ  በህግ ማስጠየቅ የለበትም የሚል አቋም ያላቸው አንዳንድ የተቋዋሚ ፓርቲ አመራሮች አሉ።  እንደዚህ ያለ እምነት ያላቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች አገራችን ለጀመረችው የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ የሚያበረክቱት አስተዋጿኦ እዚህ ግባ የሚባል አይሆንም።

ሌላው ማንሳት የምፈልገው ጉዳይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አሸባሪነት የአለማችን ስጋት መሆኑን አሌ የማይባል ጉዳይ ነው። የኢትዮጵያ መንግስት የሽብርተኝነት መንጭ የሚሆነውን አክራሪነት ለመዋጋት "ሳይቃጠል በቅጠል" እንደሚባለው   እየሰራ ባለበት በአሁኑ ወቅት አንደንድ ተቃሚ ሃይሎች የፖለቲካ ትርፍ ያስገኝልናል በማለት እጅግ የወረደ አካሄድን ሲከተሉ ይታያሉ።

በአገራችን የሃይማኖቶች ነጻነት እንዲሁም መንግስትና ሃይማኖት የተለያዩ መሆናቸው በህገ-መንግስቱ በግልፅ ተደንግጎ ሳለ አንዳንደ ተቃዋሚ ሃይሎች የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት ሲሉ ሃይማኖትንና ፖለቲካን ሲያቀላቅሉት ይታያሉ። እውነት እንናገር ከተባለ እንደ ኢህአዴግ ለሃይማኖቶች ነጻነት የታገለ ፓርቲ አለን? አንዳንድ የተቃዋሚ የፖለቲካ ሃይሎች በተለይ ሰማያዊና አንድነት  የእስልምና እምነት ተቆርቋሪዎች በመምሰል  በሃይማኖቱ ላይ መንግስት ወይም ሌላ አካል ጫና እንዳደረገበት በማስመሰል በስፋት ሲደሰኩሩ ይደመጣሉ፡፡

እነዚህ የተቃዋሚ የፖለቲካ ሃይሎች የአክራሪ ሃይሎችን ጥያቄዎች በማሰማመርና በማስጌጥ የእስልምና ሃይማኖት ላይ መንግስት ጫና እንዳደረገበት በማስመሰል በየመድረኩና በየሰላማዊ ሰልፉ ላይ ሲያናፍሱት ነበር። ፓርቲዎቹ ይህን ያደርጉ የነበሩት እውነትም ለሃይማኖቱ ተቆርቁረው እንዳልሆነ መገንዘቡ የሚከበድ አይመስለኝም። " **የበግ ለምድ የለበሰች…**" እንደሚባለው አባባል እንጂ፡፡ የሰማያዊና አንድነት ፓርቲዎችን ድብቅ አጀንዳ ዘግይቶም ቢሆን የተረዳው ብዙሃኑ ሙስሊሙ ማህበረሰብ የእነዚህን ፓርቲዎች እኩይ  እንቅስቃሴ ካባ መበግፈፍ ሴራቸውን እርቃኑን  አስቀርተውታል።

የአገራችን ተቃዋሚ ፓርቲዎች መንግስትን ለመኮነን የሚያነሱት የቅርቡ ነጠላ ዜማ  ደግሞ ከሳዑዲ አረቢያ ተመላሽ ዜጎችን ጉዳይ ነበር። የአትዮጵያ መንግስት ከሳውዲ አረቢያ ለሚመለሱ ዜጎቻችንን ለመደገፍ አቅም በፈቀደ ሁኔታ እየሰራ መሆኑን ማንም ቅን አስተሳሰብ ያለው ዜጋ ሊክደው የማይችል ሃቅ ነው። ይሁንና የአገራችንን ተቃዋሚ ፓርቲዎች  ይህን የመንግስት ጥረት

በማንኳሰስ መንግስት ለዜጎች ደንታ ቢስ እንደሆነ አድርጎ ለማቅረብ መሞከራቸው ከትዝብት ላይ የሚጥል አካሄድ ይመስለኛል።

ተቃዋሚ ፓርቲዎች በቀናነትና ለአገርና ዜጎቻች መብት ለመታገል ብለው ይህን ጉዳይ አንስተውት ቢሆን ኖሮ ነገሩ ባልከፋ። እውነታው ግን ይህ አይደለም። እውነታው የመንግስትን ጥረት በማንኳሰስ መንግስት የህዝቡን ድጋፍ እንዳያገኝ ያደርገዋል በሚል ከተንሸዋረረና ቅንነት ከጎደለው አስተሳሰብ የመነጨ አካሄድ መሆኑ ነው።

እነዚህ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ነገሩን ከቅንነትና የዜጎችን ችግር ለመጋራት አስበውት ቢሆን ኖሮ መንግስትና ዜጎች እያደረጉት ካሉት ጥረት ጎን በመሰለፍ የተቻላቸውን ያህል ድጋፍ ማድረግ በቻሉ ነበር። የእነሱ ብቸኛ አላማ በአገራችን የፀረ-አረብ ስሜት በማነሳሳት በግርግር የተሻለ ነገር ልናገኝ እንችላለን በሚል የተሳሳተ ቀመር በመነሳት እንጂ። ለተመላሽ ዘጎቻችን የቁሳቁስና የገንዘብ ድጋፍ ከማሰባሳበ ይልቅ አንድነትና ሰማያዊ ፓርቲዎች የመረጡት ለነውጥ እንዲያመቻቸው የተቃውሞ ሰልፍ ማደራጀትና ጎዳና ላይ መጮህ ነው።

የዜጎቹን መንገላታት የሚፈልግ መንግስት ያለ አይመስለኝም። በሳውዲ አረቢያ የቀሩት ዜጎቻችን ቁጥር ምንአልባት ከተመላሹ ቁጥር ሁለት ውይም ሶስት እጥፍ የሚልቅ ሆኖ ሳለ የእኛ አገር ተቃዋሚ ፓርቲዎች በአገራችን የፀረ-አረብ ስሜት እነዲቀሰቀስ መፈለጋቸው አርቆ ካለማሰብ የመነጨ ይመስለኛል። ዲፕሎማሲ ስራ የማይታያቸውና አርቀው ማሰብ የተሳናቸው የአገራችን ተቃዋሚ ፓርቲዎች አካሄዳቸው ሁሉ የጠፉት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

የኢትዮጵያ መንግስት የጎረቤት አገራት ስደተኞችን አቅሙ በፈቀደው ነገር ሁሉ በመርዳት ዛሬ አገራችን በአፍሪካ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ስደተኛን በማስተናገድና ለስደተኞች ምቹ አገር መባሏን አለም አቀፉ የቀይ መስቀል ማህበር ሰሞኑን የወጣውን ሪፖርት መመልከት ተገቢ ይመስለኛል። በሪፖርቱ ላይ አገራችን ከስድስት ሀገራት ለተውጣጡ ከሁለት መቶ ሀምሳ ሺ በላይ የሚሆኑ ስደተኞችን ተቀብላ በማስተናገዷ በአፍሪካ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውን ስደተኞች በመቀበል ቀዳማዊ እንደሆነች የሚያሳይ ነው፡፡ አገራችን በምትከተለው ትክክለኛ የውጭ ፖሊሲ በመተግበሯ ለስደተኞች ተመራጭ እንድትሆን ያስቻለው በኢህአዴግ መንግስት በሳል የዲፕሎማሲ ስራ መሆኑን መዘንጋት የለበትም። የኢህአዴግ መንግስት እንኳን ለራሱ ዜጎቹ ይቅርና ለጎረቤት አገራት ዜጎች የሚያመች የውጭ ፖሊሲ እንደሚተገበር ከዚህ ሪፖርት መረዳት ይቻላል።

ሌላው የአገራችን ተቃዋሚዎችና አጋሮቻቸው የሆኑት እነሲፒጄና ድንብር የለሹ የጋዜጠኞች ቡድን የሚያራግቡት ነገር  በኢትዮጵያ የፕሬስ ነጻነት እንደሌለ በማስመሰል የሚያቀርቡት ጉዳይ ነው። ሲፒጄ ያለምንም የተጨበጥ መረጃ ወይም የማጣራት ስራ ሳያከናውን እንደው በግርድፉ ከተቃዋሚ ፓርቲ ልሳኖቹ በደረሰው መረጃ ብቻ  ተከታታይ ሃሰተኛ ሪፖርቶችን ማውጣቱ የድርጅቱን ተራነት የሚያሳይ ነው።

ሲፒጄ የተለየ የፖለቲካ አጀንዳ ያለው ተቋም መሆኑ እንጂ እውነትም  የኢትዮጵያ ፕሬስ እንዲያድግ የሚፈልግ ተቋም  ቢሆን ኖሮ በአስር ሺህ ኪሎ ሜትሮች ላይ ሆና በስማበለው በሰበሰበው መረጃ ላይ ላይ በመንጠልጠል እንዲህ አይነት የተዛባ ሪፖርቶችን አያወጣም ነበር። ሲፒጄ የወሬ ምንጮቹን በገሃድ ባይናገራቸውም  እነማን እንደሆኑ የአደባባይ ሚስጢር ነው።

በሶስተኛው አገራቀፍ ምርጫ ወቅት የቅንጅት ዋንኛ አቀንቃኝ የሆኑ ግለሰቦች የሂውማን ራይትስ ዎች የአፍሪካ ዴስክ ኃላፊ በሆኑበት ሁኔታ  ድርጅቱ ስለኢትዮጵያ ትክክለኛ መረጃ ሊያወጣ ከቶ አይቻለውም። ገለልተኛነት በሌላቸውና ችግር ላይ በወደቁ ግለሰቦች የሚሰበሰቡ መረጃዎችና የሚቀናበሩ ሪፖረቶች እውነታነት ሊኖራቸው አይችልም። ኢትዮጵያ ከጋዜጠኝነት ስራ ጋር በተያያዘ ያሰረችው አንድም ጋዜጠኛ አለመኖሩ እየታወቀ ሆን ተብሎ የአገሪቱን ስም የማጥፋት ዘመቻ  መክፈት ድብቅ ፍላጎት መኖሩን ለመረዳት የሚከበድ አይመስለኝም። ሂዩማን ራይትስ ዎች አምነስቲን፣ አምንስቲ  ሲፒጄን፣ ሲፒጄ ሂዩማን ራይትስ ዎችን፣ ወዘተ እየተቀባበሉ የሃሰት ውንጀላቸውን ማራገባቸው ድብቅ የፖለቲካ አጀንዳ እንዳላቸው  ለመረዳት ምርምር ማድረግ የሚያስፈልግ አይመስለኝም።

ይህንኑ ጉዳይ በተመለከተ ባለፈው ሳምንት ለህትመት በበቃ አዲስ አድማስ ጋዜጣ ላይ ያነበብኩትን አስገራሚ ነገር ላካፍላችሁ።  በቅርቡ ሲፒጄ ባወጣው  ሪፖርት ዙሪያ አስተያየታቸውን የሰጡት የመድረክ መሪ  ዶ/ር መረራ  እንዳሉት መንግስት ጋዜጠኞችን እንደሚያስር ለማረጋገጥ ከፈለጋችሁ እስር ቤት ሄዳችሁ መመልከት ትችላላችሁ ብለዋል። ይህ የዶክተር መራራ አባባል ጋዜጠኛ ምንም አይነት ወንጀል ቢሰራ መታሰር የለበትም  የሚል መልዕክት የሚያስተላልፍ ሆኖ አግኝቼዋለሁ።

መንግስት በተደጋጋሚ እየገለፀ ያለው በጻፈው ወይም ከጋዜጠኝነት ስራው ጋር በተያያዘ ለእስር የተዳረገ አንድም ጋዜጠኛ የለም  እንጂ  በተለያየ ጉዳይ የታሰረ ጋዜጠኛማ  በእስር ላይ ሊገኝ ይችላል። ማንም ከህግ በላይ  ሊሆን  አይችሉም። የህግ የበላይነት የሚባለው ሁሉም ለሰራው ጥፋት እኩል ህግ ፊት ሲቆም ነው። እነ ዶክተር መራራና አጋሮቻቸው ታዲያ  መንግስት ጋዜጠኛ

አላሰርኩም የሚለውን ነገር ማረጋገጥ ከፈለጋችሁ እስር ቤቶችን መጎብኘት ነው በማለት መከራከሪያ ነጥቡን ወይም አርጊዩመንቱን ለወጥ በማድረግ አቅርበውታል።

ሌላ አንድ ለየት ያለ አስቂኝ አቤቱታ ላካፍላችሁ። የባለፈው ሳምንት ለህትምት የበቃ ኢትዮ ምህዳር ጋዜጣ ላይ የመኢአድ ክስን መመልከት የአገራችን ተቃዋሚ ፓርቲዎች የሚያነሷቸው አቤቱታዎች ምን ያህል የወረዱና ታአማኒነት የጎደላቸው እንደሆኑ መመልከት ጠቃሚ ይመስለኛል። ሰሞኑን በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ ሶስት በተለምዶ ሀዲድ ሰፈር በሚባለው አካባቢ ለሚገነባው የብሄራዊ ስታዲዮም ግንባታ ሲባል የግለሰቦች መኖሪያ ቤቶች እየፈረሱ መሆኑን ተከትሎ መኢአድ የአባላቶቼ መኖሪያ ቤቶች በዘመቻ እየፈረሱ ነው በማለት አቤቱታ አሰምቷል፡፡

ይህ የመኢአድ አካሄድ እጅግ የወረደ መሆኑን መገንዘብ የሚከብድ አይመስለኝም። በቅድሚያ መንግስት ሆን ብሎ የመኢአድ አባላት መኖሪያ አካባቢ ስታዲዮም ለመገንባት እንደተነሳና የመኢአድን አባለት መኖሪያ ቤቶችን ብቻ ተለይተው እንዲፈረሱ ተደርጓል ማለት ፓርቲው ምን ያህል ትንሽ እንደሆነ ጥሩ ማሳያ ነው።

የመኢአድ አባል ሆኑም አልሆኑም፣ የኢህአዴግ አባል ሆኑም አልሆኑም በአጠቃላይ የማንኛውም ፓርቲ አባል ሆኑም አልሆኑም፣ መንግስት በልማት ሳቢያ ለተፈናቀሉ ዜጎች ሁሉ እንደየፍላጎታቸው ተለዋጭ ነገር እያቀረበ እንደሆነ አፍ ሞልቶ መናገር ይቻላል። አብዛኛው ነባር የከተማዋ ክፍሎች ፈርሶ እንደ አዲስ እየተገነባ ባለበት ሁኔታ ይነስም ይብዛም የነዋሪዎቿን አስተዋጾዖን መጠየቁ የግድ መሆኑ እየታወቀ እንደ መኢአድ ያሉ ፓርቲዎች እንዲህ ያሉ አሉባልታዎችን በመንዛታቸው የሚያገኙት ትርፍ መናኛ መሆኑን መገንዘብ አለባቸው።

ተመሳሳይ መናኛ ምክንያቶችን የሚያነፈንፈው የአንድነት ለዴሞክራሲና ፍትህ ፓርቲ በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች በምንም ምክንያት ብቻ የሞተን ወይም የታሰረን ግለሰቦችን ስም በማፈላለግ በደቂቃ ውስጥ አባለቶቼ በማድረግ ለሃሰት ውንጀላው ይጠቀምበታል። እንዲህ ያሉ ነገሮችን በማቀነባበር የሚታወቀው አንድነት ፓርቲ አባላቶቼና ደጋፊዎቼ በገዥው ፓርቲ ካድሬዎች ተገደሉ፣ ታሰሩ ውይም ተደበደቡ በማለት የሃሰት ውንጀላዎችን መደርደር ይወዳል። ይህ አይነት አካሄድ አገራችን በ2007 ዓ.ም ለምታካሂደው አጠቃላይ ምርጫ ላይ ኢህአዴግን ለመወንጀል እንዲያመች መደላድል ለመፍጠር እንደሆነ በቀላሉ መረዳት ይቻላል።

ሌላ አንድ ነገር ላንሳላችሁ። የአገራችን የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮችና ሊሂቁዎቻቸው የፓርቲዎቻቸውን የውስጥ ችግር ለማከም የመረዳቸውን መደሃነት ከማፈላለግ ይልቅ በኢህአዴግ የውስጥ አሰራር በመግባት ሲዘላብዱ ተመልክተናል። ለዚህ አንድ ማሳያ ሰሞኑን አቶ አያሌው ጎበዜን ከአማራ ክልል ፕሬዚዳንትነት ወደ ቱርክ የኢትዮጵያ አምባሳደር ተደርገው መሾማቸውን ተከትሎ የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮችና ሊሂቁዎቻቸው የሚሰጡት ትንታኔ እጅግ አስገራሚ ነው።

መንግስት የኢትዮጵያን መሬት ለሱዳን አሳልፎ ለመስጠት እነዲያመቸው ሲል አቶ አያሌው ጎበዜን ከፕሬዝዳንትነታቸው መነሳት በማስፈለጉ ምክንያት ብአዴን ይህን እርምጃ እንዲወስድ ተገዷል ሲሉ ተደምጠዋል። የተባለውን መሬት ኢትዮጵያ ለሱዳን መስጠት እንኳን ካለባት የሚወስነው የፌዴራል መንግስቱ ደረጃ እንጂ በክልል ደረጃ ሊሆን ከቶ አይቻለውም። ኢትዮጵያና ሱዳን የድንበር አከላለልን በተመለከተ የሁለቱ አገራት መንግስታት አለም አቀፍ ስምምነቶችና መርሆች ላይ ተመስርተው የሚያካሂዱት ነገር እንጂ እንደው በዘፈቀደ የሚከናወን ነገር ሊሆን አይችልም። እውነታው ይህ ሆኖ ሳለ የእኛ አገር የፖለቲካ ሊቅ ነን ባዮች ትንታኔ እጅግ የሚገርም ነው።

እንግዲህ የአገራችን ተቃዋሚ ፓርቲዎች ህዝብን ሊጠቅም የሚችል የተሻለ ፖሊሲና ስትራቴጂ ነድፎ መንግስትን መሞነት ሲሳናቸው እንዲህ ያሉ የወረዱ ነገሮችን በማፈላለግ ላይ መጠመዳቸው የፓርቲዎቹን በምርጫ አሸናፊ ሆኖ አገር የመምራት አቅም የት ድርስ እንደሆነ የሚያሳይ ጉዳይ ነው።